# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ

## ትምህርት ሚኒስቴር

## ግንቦት 2013 ዓ.ም

## አዲስ አበባ

**ማውጫ**

**ክፍል አንድ** ..... 4

1. **አጠቃላይ ጉዳዮች** ..... 4

   1.1. መግቢያ ..... 4

   1.2. **የቃላት መፍቻ** ..... 5

   1.3. **የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ** ..... 7

   1.4. **የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲው አስፈላጊነት መነሻዎች** ..... 9

      1.4.1. **የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ቁልፍ የሰብዓዊ ሀብት ልማት አጀንዳ ስለሆነ፡-** ..... 10

      1.4.2. ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ድንጋጌዎች፣ ህግመንግስታችን እና አገራዊ ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎቻችን እንደመነሻ፣ ..... 11

      1.4.3. ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀትን ለመፍጠር፡- ..... 12

   1.5. **የፖሊሲው መሰረታዊ አቅጣጫዎች** ..... 12

   1.6. **የፖሊሲ ማዕቀፍ** ..... 14

**ክፍል ሁለት** ..... 15

2. **የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማዎችና ምሰሶዎች (Pillars)** ..... 15

   2.1. **የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማዎች እና የተፈጻሚነት ወሰን** ..... 15

      2.1.1. **የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ** ..... 15

      2.1.2. **የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ተልዕኮ** ..... 15

      2.1.3. **ግብ** ..... 16

      2.1.4. **የፖሊሲው ዋና ዓላማ** ..... 16

      2.1.5. **ዝርዝር ዓላማዎች** ..... 16

   2.2. **የፖሊሲው ወሰን** ..... 16

   2.3. **የፖሊሲው ተጠቃሚዎች** ..... 17

   2.4. **የፖሊሲው እሴቶችና መርሆዎች** ..... 17

   2.5. **የፖሊሲው መሰረታዊ ምሰሶዎች/Policy Pillars)** ..... 18

**ክፍል ሦስት** ..... 19

**3. የፖሊሲ ጉዳዮች፣ አቅጣጫዎችና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች** ........ 19

**3.1. የፖሊሲ ጉዳይ አንድ ፡- ለሀገር በቀል ምርቶች ትኩረት በመስጠት ሁሉም የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ የተመጣጠነና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ ማግኘት አለባቸው።** ........ 19

**3.2. የፖሊሲ ጉዳይ ሁለት ፡ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጠራል፣ የአቅም ግንባታና ግንዛቤ ማሳደጊያ ስራ ይከናወናል፤** ........ 23

**3.3. ፖሊሲ ጉዳይ ሶስት፡- ዘላቂ የበጀት ምንጭን ማረጋገጥ** ........ 24

3.4. ፖሊሲ ጉዳይ አራት፡- ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአቶችን መዘርጋት፣ ........ 26

**ክፍል አራት** ........ 28

**4. የምግብ ይዘትና ግዢ ስርዓት** ........ 28

**4.1. የምግብ ይዘት** ........ 28

**4.2. የግዥ ስርአት** ........ 28

ክፍል አምስት ........ 31

**5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ፈጻሚ ተቋማትና የባለድርሻ አካላት ሚና** ........ 31

5.1. የትምህርት ሴክተር ተግባርና ኃላፊነት ........ 32

5.2. **የሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች** ........ 36

5.3. **የክልል መንግስታት** ........ 41

5.4. የአጋር ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ ........ 42

**ክፍል ስድስት** ........ 44

**6. የክትትልና ግምገማ ስርአት** ........ 44

# ክፍል አንድ

# 1. አጠቃላይ ጉዳዮች

## 1.1. መግቢያ

ትምህርት ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ በትምህርት ላይ የሚደረግ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ትርፉ ብልፅግና ነው። የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተገቢውን ትኩረት አግኝቶና በቂ ፋይናንስ ተመድቦለት ከተተገበረ የሚገኘው የብልፅግና ትሩፋት በተሰራው ስራ መጠን መሆኑ ይታወቃል። ይህንን ዘርፈ ብዙ ጥቅም በመረዳት እ.ኤ.አ በ1948 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወጣው የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች ትምህርት ማግኘት የሰብኣዊ መብት ጉዳይ መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል።

በሀገራችን ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱት መካካል ከ26.8 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ልጆች ከ40,000 በላይ በሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ (EMIS 2012ዓ/ም)። እድሜያቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረሱ ሁሉንም ልጆች ተደራሽ ለማድረግ በተደረጉ ጥረቶች አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ልጆች ዛሬም ድረስ ከትምህርት ገበታ ውጪ መሆናቸውን በርካታ መረጃዎች ያሳያሉ።

ለትምህርት ተሳትፎ እና ውስጣዊ ብቃት ችግር ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የምግብና ስርአተ ምግብ ጉድለት እንደሆነ ይታወቃል። ልጆች ለምግብ እጥረት በመጋለጣቸው የተነሳ ከምግብ እጥረት ጋር ተያይዞ ለሚመጣው አካላዊና አዕምሮአዊ ዕድገት ውስንነት ተጋላጭ እንደሆኑ ይታመናል።

በአንፃሩ በተሟላ የአመጋገብ ሥርዓት ያደጉ ልጆች የትምህርት ተሳትፎና የሚያስመዘግቡት የትምህርት ውጤት ከፍተኛ ሲሆን ያላቸውን ዕምቅ አቅም ሥራ ላይ የማዋልና ጥረትን የማሳካት ዕድላቸውም ከፍተኛ እንደሚሆን ይታወቃል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን መተግበር ለትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ችግሮች ቁልፍ የመፍቻ መንገድ ሆኖ ይወሰዳል። ሀገራችን በትምህርት ስርአቱ ላይ እያጋጠሟት ያሉትን የትምህርት ተሳትፎ፣ ፍትሃዊነትና ተጠቃሚነት፣ ብክነትና ጥራት ችግሮችን እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ የሚስተዋለውን የሥርዓተ-ምግብ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ

ጉዳዩ በሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ቅንጅት፣ ትብብርና ተሳትፎ ሊያጠናክርና አስተዋፅኦቸውን ሊያሳድግ በሚችል መልኩ እንዲተገበር ታሳቢ ተደርጎ ይህ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ፖሊሲዉና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂው በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ ክፍል አንድ መግቢያና አጠቃላይ ሁኔታ የያዘ ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ የፖሊሲው ራዕይ፣ ግብ፣ ዓላማዎችና የፖሊሲ ምሰሶዎች ተገልጸዋል፡፡ በክፍል ሶስት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በክፍል አራት ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚውለውን የምግብ ይዘትና ግዢ ሥርዓት የያዘ ሲሆን በክፍል አምስት የፖሊሲው ፈጻሚ ተቋማት ሚና ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም የፖሊሲና ስትራቴጂው የክትትልና ግምገማ ዘዴ በክፍል ስድስት ተመላክቷል፡፡

## 1.2. የቃላት መፍቻ

በዚህ ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ማዕቀፍ መሰረት፣

1. **"ትምህርት ቤት"** ማለት በመንግስት፣ በግል እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደርና የቅድመ አንደኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1ኛ- 8ኛ ክፍል) ተማሪዎች የሚማሩበት ተቋም ማለት ነው፡፡
2. **"ተማሪዎች"** ማለት በቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ህጻናትና ወጣቶች ማለት ነው ፡፡
3. **"ሀገር በቀል ትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር"** ማለት ምግብን ከሀገር ውስጥ ከሚበቅሉ የእህል አይነቶች እና የምግብ ማጣፈጫዎች አዘጋጅቶ በማቅረብ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን መመገብ ወይም የተመጣጠነ ምግብ መስጠት ማለት ነው፡፡
4. **"የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር"** ማለት የተመጣጠነና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብን በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች አዘጋጅቶ መስጠት ማለት ነው፡፡
5. **"ምግብ" ማለት** ለተማሪዎች አገልግሎት እንዲበላና እንዲጠጣ የተፈቀደ ነው፡፡
6. **"ሥርዓተ-ምግብ"** ማለት የምግብ መመገብን፣ የምግብ መፈጨትን፣ ምግብ በሰውነት ውስጥ መዋሃድንና የንጥረ-ምግቦች ጥቅም ላይ መዋልና ሂደቱ አካላዊና አዕምሮአዊ ዕድገትና ብልፅግን፣ በሽታ መከላከልና መቋቋምን ያካተተ ነው፡፡

7. **"ንጥረ-ምግብ"** — በምግብ ውስጥ የሚገኙ ኬሚካሎች ሲሆኑ ለሰውነት ሀይል፣ ለህዋሶች መታደስ፣ በሰውነት ውስጥ የሚገኙ ቅመሞች በትክክል እንዲሰሩና ትክክለኛ የሰውነት እድገት እንዲኖር ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ በምግብ ውስጥ የሚገኙ ንጥረ-ነገሮች ናቸው።

8. **"ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና"** — ሁሉም ሰው በማንኛውም ጊዜ ፍላጎቱንና ምርጫውን የሚያሟላ ጤነኛና ብሩህ ህይወት እንዲኖረው ጥራቱን የጠበቀና በአይነት፤ በስብጥር፤ በደህንነትና በንጥረ-ምግብ ይዘቱ በቂ የሆነ ምግብ የማግኘት እንዲሁም በቂ የጤና እንክብካቤ፤ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና ጽዱ የመኖሪያ አካባቢ፤ በቤተሰብና ማህበረሰብ ደረጃ ስለ ሕጻናት ክብካቤ፤ ስለ ምግብ አዘገጃጀትና አያያዝ በቂ እውቀት የማግኘት ሁኔታ ማለት ነው።

9. **"ምግብ ዋስትና"** — የምግብ ዋስትና ማለት ሁሉም ሰው ጥራት ያለውና ጤነኛ ህይወት ለመምራት እንዲሁም የቀን የምግብ ፍላጎቱንና የምግብ ምርጫውን የሚያሟላ በቂ፤ የተመጣጠነና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ በማንኛውም ጊዜ ለማግኘት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተደራሽነት ሲኖረው ነው።

## 1.3. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ

የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ችግር በልጆች ጤና፣ የመማርና የማሰብ ችሎታ ላይ ተጽዕኖው የከፋ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በኢትዮጵያ 16% የሚሆነው የተማሪዎች መጠነ መድገም ከተመጣጠነ ምግብ ችግር ጋር የተያያዘ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ (COHA 2009)፡፡ እንዲሁም የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ክስተት በተማሪዎች ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል (ትምህርት ሚኒስቴር 2012)፡፡ ከተመጣጠነ ምግብ እጥረትና ከአጭር ጊዜ ረሀብ ጋር ተያይዞ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ስለሚያቋርጡ በርካታ የትምህርት ቀናቶች ይባክናሉ፡፡ በተለይም ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች ምግብ ሳይመገቡ ወደ ትምህርት ቤት እንደሚሄዱም ይታመናል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የትምህርት ቤት ምገባ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደቁልፍ መፍትሄ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

በታሪክ ሰነድ የተቀመጠ መረጃ ባይኖርም የትምህርት ቤት ምገባ በንጉሱ ዘመን በሀገራችን ይካሄድ እንደነበረ የአፈ-ታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ በትላልቅ ከተሞች የሚገኙ ጥቂት ወላጆች ለልጆቻቸው በትምህርት ቤት እንዲመገቡት ቋጥረው ከሚልኩት ምግብና ውስን ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ከሚያካሂዱት የትምህርት ቤት ምገባ በስተቀር ጎልቶ ሊጠቀስ የሚችል የትምህርት ቤት ምገባ በሀገራችን አልነበረም፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በሀገራችን በይፋ የተጀመረው ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ዓላማውም ምግብ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ መርሃ ግብሩም የተጀመረው በዓለም ምግብ ፕሮግራም /UNWFP/ እና በትምህርት ሚኒስቴር ትብብር በአራት ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ አፋርና ኦሮሚያ) በ40 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከውጭ ሀገር ተገዝቶ በሚቀርብ ምግብ ነው፡፡ መርሃ ግብሩ እንደተጀመረ 25,000 ልጆች የምገባ ተጠቃሚ መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

መርሃ-ግብሩ ተሞክሮ ባመጣው ተስፋ ሰጭ ውጤት ወደ ሌሎች ክልሎችም (ደቡብና ሶማሌ) ተስፋፍቶ እ.አ.አ ከ2004-2006 ዓ.ም ድረስ በ1200 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ 649,000 ተማሪዎችን እስከ መመገብ ተደርሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ የልጃገረዶችን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ ያለሙ ድጋፎች (Take-home rations conditional to school attendance Initiatives) ማካተት ተችሏል፡፡ በተለያየ ጊዜ በተሰሩ የዳሰሳ ጥናቶች እነዚህ ፕሮግራሞች በመተግበራቸው የተማሪዎች ተሳትፎ ከመጨመሩም በላይ፣ መጠነ ማቋረጥና መቅረትን በመቀነስ በትምህርት ጥራት ላይ መርሃ-ግብሩ የራሱን አዎንታዊ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

ሆኖም የምገባ አገልግሎቱ ተፈላጊነት እየጨመረ ሲመጣ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ከለጋሾች ይገኝ የነበረው እርዳታ እያሽቆለቆለ በመምጣቱና ከመንግስት በጀትም ድጋፍ ስላልነበረው አገልግሎቱን የሚያገኙ ተማሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ በመምጣቱ ትኩረቱንም እንደ አፋርና ሶማሌ ባሉ አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ብቻ ለመወሰን ተገደደ፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን ዘላቂና ሀገር በቀል አድርጎ ለማስቀጠል እ.አ.አ 2012 ዓ.ም የትምህርት ቤት ልጆችን በሀገር ውስጥ በተመረተ ምርት የመመገብ የሙከራ ፕሮጀክት ከዓለም ምግብ ፕሮግራምና ሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር በደቡብ ክልል በ 37 ትምህርት ቤቶች የተተገበረ ሲሆን በውጤቱም የትራንስፖርትና ምግብ ግዥ ዋጋ ቆጣቢ፣ የአካባቢውን አርሶ አደር ምርት ገበያ የሚያነቃቃና ልጆችም የሚያውቁትን የአካባቢያቸውን ምግብ እንዲመገቡ እድል የፈጠረ በመሆኑ ተሞክሮው ወደ ኦሮሚያና ሌሎች ክልሎች ተስፋፋ፡፡ እንደ ደቡብና ኦሮሚያ ያሉ ክልሎችም በጀት በመመደብ ከዓለም ምግብ ፕሮግራም ጋር በቅንጅት መስራት ጀመሩ፡፡

በተጨማሪም የመንግስትን ጥረት የሚደግፉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚተገብሩ ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (ኢትዮጵያ ስኩል ሚል ኢኒሼቲቭ፣ የእናት ወግ በጎ አድራጎት ማህበር እና ሌሎች) በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ እነዚህም ፕሮጀክቶች ጥሩ ውጤት የተመዘገበባቸው እና ለቀጣይ ሀገራዊ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ- ግብር ትግበራ ልምድ የተወሰደባቸው ናቸው፡፡

ከዚህም ሌላ ከ2007/2008 ዓ.ም ጀምሮ ሀገራችን የገጠማት ድርቅ በትምህርት ሴክተሩ ላይ ያስከተለውን አደጋ ለመቀልበስ በፌደራል መንግስትና በክልሎች መደበኛ በጀት የተጀመረው የአስቸኳይ ጊዜ የትምርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርም የሀገር በቀል የምገባ ሞዴልን (Home-grown school feeding) አሰራርን በመጠቀም በ2008 ዓ.ም ከ3 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን መመገብ ከመቻሉ በላይ በርካታ የስራ እድልና ለአርሶ አደሩና ለህብረት ስራ ዩኒየኖች ገበያ መፍጠር መቻሉ ተረጋግጧል፡፡

በዚሁ መነሻ የፌደራል እና የክልል መንግስታት በሚመድቡት በጀት የአስቸኳይ ጊዜ ምገባ ፕሮግራምን በአብዛኞቹ ክልሎች ማስቀጠል የተቻለ ሲሆን በአንዳንድ ክልሎችም ለምገባ መርሃ-ግብሩ ቋሚ መደበኛ በጀት ተመድቦ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በ2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በሀገሪቱ ከ1.6 ሚሊየን በላይ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ላይ እንዳሉ መረጃዎች ሲያሳዩ እንደ አዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር ያሉት የተማሪዎች ምገባ መርሃ-ግብርን በኤጀንሲ ደረጃ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር በሁሉም የመንግስት ትምህርት ቤቶች ላሉ የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጆች ምግብ ማቅረብ የተቻለ ቢሆንም አሁንም የሀገራችን የትምህርት ቤት የምገባ ሽፋን እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ምገባ ወጭ ሳይሆን በመጭው ሀገር ተረካቢ ትውልድ ላይ የሚደረግ አዋጭና ዘላቂ የሰብአዊ ልማት ኢንቨስትመንት እንደሆነ በከፍተኛ ሁኔታ እየታመነበት በመምጣቱና ከሀገር ኢኮኖሚና ከማህበራዊ ጉዳዮች ጋር ያለው መስተጋብርም ጉልህ በመሆኑ በሀገር ደረጃ ተግባራዊ ቢደረግ ትልቅ የልማት አቅም ስለሆነ ሀገር አቀፍ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ነድፎ፣ በበጀትና መዋቅራዊ አደረጃጀቶች ደግፎ መንቀሳቀስ ለነገ የማይባል አብይ ጉዳይ ነው።

## 1.4. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲው አስፈላጊነት መነሻዎች

የትምህርት ቤት ምገባ በሁሉም የዓለም ሀገሮች ሊባል በሚችል መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ ፕሮግራም ሲሆን በተለይም በሀብት በበለፀጉት አገሮች ውስጥ ያለው ተደራሽነት ከፍተኛ ነው። እ.ኤ.አ በ2020 በዓለም ምግብ ፕሮግራም በተጠናው ጥናት እንደተመለከተው በዓለም ላይ በ161 ሀገራት የሚገኙ ከ388 ሚሊዮን በላይ ልጆች የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብር ተጠቃሚ መሆናቸውና በልጆች ላይ አንድ ዶላር ሀብት ማፍሰስ ወደ ዘጠኝ ዶላር ትርፍ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከስራ እድል ፈጠራ አኳያ ደግሞ አንድ መቶ ሺህ ልጆችን የመመገብ መርሃ-ግብር ለ1668 ወጣቶችና እናቶች የስራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል(State of School Feeding World Wide 2020 WFP)፡፡ በአጠቃላይ የምገባ ፕሮግራሙ ለመማር ማስተማሩና ለተማሪዎች እንዲሁም ለሌሎች ሴክተሮች የሚያበረክተው ዘርፈ ብዙ አስተዋፅዖ  የላቀ መሆኑን ያሳያል፡፡

የዓለም ምግብ ፕሮግራም  እ.አ.አ 2017 ዓ.ም  ከ Master of Card Foundation ጋር በመሆን በኢትዮጵያ ባጠናው ጥናት በሀገር በቀል ትምህርት ቤት ምገባ አማካይነት በአንድ ልጅ የትምህርት ዘመን ላይ ኢንቨስት የምትደረግ እያንዳንዷ ዶላር በህይዎት ዘመኑ/ኗ የልጁን/ቷን ትምህርት፣ጤናና ምርታማነትን በማሻሻል በአማካይ የ7.2 የአሜሪካን ዶላር ትርፍ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን በዘላቂነት መተግበር ብቃት ያለውን የበለፀገ የሰው ኃብት እንደሚያስገኝ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ፕሮግራሙ ለረሃብ ተጋላጭነትን በማስቀረት የተሟላ ሥነ-ምግብና፤ ጤና እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ የተሻለ የትምህርት ተሳትፎ፣ አቀባበል እና ውጤት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም ይህ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ መንግሥት ከፍተኛውን የአመራር ባለቤትነት ይዞ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አቀናጅቶና አደራጅቶ የሚመራበት የፖሊሲ ማዕቀፍ መፍጠርና ሀገሪቱ እያጋጠሟት ያሉትን የምግብና ሥርዓት- ምግብ ዋስትና ተግዳሮቶች በትምህርት ሴክተሩ ላይ ያላቸው

አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቅረፍ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን የፖሊሲ ሰነዱ መዘጋጀት አስፈላጊነትም በሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ተለይቶ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

### 1.4.1. የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ቁልፍ የሰብዓዊ ሀብት ልማት አጀንዳ ስለሆነ፦

ኢትዮጵያ በየጊዜው የተለያዩ የልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎችን አውጥታለች፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ብቁ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ምክንያት እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የታሰበላቸውን የልማት ስኬት በማምጣት ዙሪያ የማስፈጸም አቅም ውስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡

ባለፉት አመታት በሀገራችን በትላልቅ ግድቦች፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በሌሎችም መሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ኢንቨስት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ ነገር ግን በሰብዓዊ ልማት ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት አብሮ ካላደገ ሁለንተናዊ እድገትን ማረጋገጥ እንደማይቻል ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ለረሃብ ተጋላጭነትን በማስቀረት የተሟላ ሥነ-ምግብና፤ ጤና እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ የተሻለ የትምህርት አቀባበልና ውጤት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ የተመጣጠነ ምግብ አግኝተው ያደጉ ህፃናት ከሌሎች ህፃናት ጋር ሲወዳደሩ የበለጠ ጤናማ፣ በትምህርታቸው ውጤታማ በተለይም በሂሳብና በሳይንስ ትምህርቶች የላቀ ችሎታ ያላቸው፣ አዳዲስ ጠቃሚ ሃሳቦችን ማፍለቅ የሚችሉ፣ በጥልቀት በማሰብ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ፣ ሲያድጉም ስራ ፈላጊ ሳይሆኑ ብቁና ስራ የመፍጠር ችሎታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ልጆች ከተፀነሱበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያዎቹ 1,000 ቀናት ላይ መዋዕለ ንዋዕይ ማፍሰስ ለልጆች ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝና አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በልጆች ዘንድ የተሟላ ጤና፣አካላዊና አእምሮአዊ እድገት ለማምጣት በቀሪዎቹ 7000 ቀናት ማለትም በልጅነት እና በጉርምስና ዕድሜ ተጨማሪ ዕድሜ-ተኮር ድጋፍ ማድረግ በመጀመሪያዎቹ አንድ ሺህ ቀናት የተገኙ ውጤቶች ወደኋላ እንዳይመለሱ ከማስጠበቅ በተጨማሪ በመጀመሪያዎቹ 1000 ቀናት የነበሩ ጉድለቶችን ለማስተካከል እድል መስጠት የሚቻልበት ወሳኝ ጊዜያት ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብርን በዚህ እድሜ ክልል ላሉ ልጆች ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወት አስፈላጊ ተግባር እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡

ስለሆነም ለሰብዓዊ ሀብት ልማት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱት ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው ለውጤታማነታቸው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ቁልፍ የልማት መሳሪያ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከዚህ አንጻር መርሃ-ግብሩን መተግበር ሀገሪቱ ለተያያዘችዉ የብልጽግና ጉዞ የመጪዉን ሀገር ተረካቢ ትዉልድ ብቃት ለማረጋገጥና ታላላቅ የልማት ግቦቻችንን ለማሳካት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

መንግሥት ፕሮግራሙ የሚያመጣውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በመገንዘብ በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት አካላት በተለያዩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፤ ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም በትምህርት ፍኖተ-ካርታው ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሃገራችን ኢትዮጵያ እስከ አሁን ለፕሮግራሙ የራሱን ፖሊሲ አዘጋጅታ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በመተግበር የሚጠበቀውን ውጤት ሳታስመዘግብ ቆይታለች፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ መንግሥት ከፍተኛውን የአመራር ባለቤትነት ይዞ ሌሎች ባለድርሻ አካላትን አቀናጅቶና አደራጅቶ የሚመራበት የፖሊሲ ማዕቀፍ መፍጠርና ሀገሪቱ እያጋጠሟት ያሉትን የትምህርት ተሳትፎ፣ አካታችነትንና ውጤታማነትን እንዲሁም የምግብና ሥርዓተ- ምግብ ዋስትና ተግዳሮቶችን ለመፍታት ፖሊሲው አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 1.4.2. ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ድንጋጌዎች፣ ህግመንግስታችን እና አገራዊ ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎቻችን እንደመነሻ፣

እ.ኤ.አ. በ1989 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወጣው የህፃናት መብቶች ኮንቬንሺን ህፃናት ለህይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማለትም ምግብ፣ትምህርት፣ የጤና እንክብካቤ ወ.ዘ.ተ አግኝተው የማደግ መብት እንዳላቸው በመደንገግ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ አባል አገራት የህፃናትን ሁለንተናዊ መብቶች እንዲያስከብሩ ያስገድዳል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ይህንን የህፃናት መብቶች ስምምነትን በስራ ላይ ለማዋል እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም ተቀብላ በሀገሪቱ ህጎችና ፖሊሲዎች በማካተት በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህም መሠረት የህፃናት መብት ጉዳይ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 36፣ በወንጀል ህግ፣ በትምህርት ፖሊሲ፣ በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ በማህበራዊ ደህንነት ፖሊሲ፣ በምግብና ስርአተ ምግብ ፖሊሲ፣ በጤና ጥበቃ ፖሊሲ እና በሌሎችም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት መብቶች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው፣ ልጆች በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለጤንነታቸው ተስማሚ፣ በንጥረ ምግብ ይዘቱ የተሟላና በቂ ምግብ በማግኘት ከረሃብ ነፃ ሆኖ የመማር መብታቸው ስለሆነ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በሁሉም አካባቢዎች አደረጃጀት ተፈጥሮለት በባለቤትነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበር ፖሊሲ ያስፈልገዋል፡፡

### 1.4.3. ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀትን ለመፍጠር፡-

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ቁልፍ የልማት አጀንዳ በመሆኑ በሁሉም አካባቢዎች ብዙ ተማሪዎችን ተደራሽ በማድረግ የታሰበለትን ግብ እንዲያሳካ በየደረጃው በሚገኙ የመንግስት አመራሮች ትኩረት አግኝቶ መንግስት መደበኛ በጀት በመመደብ፣ ከአጋር አካላት ሀብት በማሰባሰብ እና ሌሎች አዋጪ የሀብት ማግኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ፕሮግራሙን ለማስፈፀም የሚያስችል ራሱን የቻለ ተጠያቂነት ያለው ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት ለመፍጠር ፖሊሲ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ መንግሥት ለሕፃናት የትምህርት ቤት ምገባን እንደ ፖሊሲ አቅጣጫ ያስቀመጠበት ምክንያት፡ የትምህርት ቤት ምገባ አንዱ የማህበረሰብ ደህንነትና ጥበቃ ዘርፍ በመሆኑ፤ ጥራት ያለው ትምህርት ፍትሃዊና ተደራሽ እንዲሆን ስለሚያግዝ፤ አርሶ አደሮች ገበያና ሥነ-ምግብ ተኮር እንዲሆኑ ስለሚያበረታታ፤ በመንግሥት የተለያዩ ዘርፎች፣ ህብረተሰቡና የግል ዘርፉ ትብብርና አጋርነት የሚፈጥር በመሆኑና መንግስትም በባለቤትነት አስፈላጊውን የበጀት ድጋፍ እያደረገ በዘላቂነት እንዲያስቀጥለው ስለታመነበት ነው፡፡

## 1.5. የፖሊሲው መሰረታዊ አቅጣጫዎች

የትምህርት ቤት ምግባ ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ የሚከተሉትን አጠቃላይ አቅጣጫዎች መሰረት አድርጎ የሚተገበር ይሆናል፡፡

I. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ በሀገሪቱ ለሚታለመው ዘላቂ የሆነ የምገባ መርሃ-ግብር ዕቅድ ትግበራ፣ አስተዳደር፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር እንዲኖር አስፈላጊ የህግና ተቋማዊ ማዕቀፍ በመፍጠር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

II. በቅድመ አንደኛና በመጀመሪያ ደረጃ የሚማሩ ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ለጤንነታቸው ተስማሚና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ እንዲያገኙ ለማስቻል የምገባ መርሃ-ግብሩን የሚመለከቱ ስትራቴጂዎች እንዲከለሱና አዳዲስ ፕሮግራሞች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

III. በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ልጃገረዶችና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ መርሃ-ግብሩ በልዩ ሁኔታ ታቅዶ ይሰራል፡፡

IV. ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚውሉ ግብአቶች ሀገር በቀል ምርቶች እንዲሆኑ ትኩረት በማድረግና ያልተማከለ አሰራርን በመጠቀም ቀላል፣ ተስማሚ፣ ቀጣይነት ያለው፣ አዋጭና

ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ሞዴሎችን በመጠቀም ዘላቂነት ያለው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

V. ከሁሉም ፈጻሚ ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ አጋር አካላትና ከማህረሰቡ ጋር የትብብርና ቅንጅታዊ አሰራሮችን ለማጠናከር የሚያስችሉ የመረጃ ልውውጥ ስርአቶች ተዘርግተው ተግባር ላይ ይውላሉ፡፡

VI. ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ትግበራ የሚያግዙ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት፣ መርሃ-ግብሩን ለማሳለጥ የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን በማሟላትና በማጠናከር፣ በመስኩ የሰለጠነ የሰው ሀይል ስምሪትና የአቅም ግንባታ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡


VII. በመንግስትም ሆነ በግል ዘርፍ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችና ኢንቨስትመንቶች በአቅራቢያቸው ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ለሚካሄደው የምገባ መርሃ-ግብር ድጋፍ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣

VIII. ለትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብር የሚውሉ ግብአቶች ከአርሶ/አርብቶ አደሮች፣ ከተደራጁ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት፣ ከህብረት ስራ ዩኒየኖች እና ከሌሎች የማህበረሰብ አደረጃጀቶች እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ይህም አሰራር የገበያ ትስስርን በመፍጠር ለእናቶች፣ ለወጣቶችና አርሶ አደሮች የስራ እድሎች በመፍጠር ገቢቸው እንዲድግ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡

IX. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን የሚተገብሩ ትምህርት ቤቶች ለአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ትኩረት በመስጠት ዘላቂ የሆነ የአረንጓዴ አሻራ ልማት ስራዎችን በመተግበር ትምህርት ቤቶችን ምቹ፣ ሳቢና ማራኪ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሠራል፡፡ በተጨማሪም ሀይል ቆጣቢ የሆኑ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአካባቢ መራቆትንና ብክለትን ለመከላከል ትኩረት ይደረጋል፡፡

X. ትምህርት ቤቶች በይዞታ መሬታቸው ውስጥ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በንጥረ ነገር የበለጸጉ ሰብሎችን በአዳዲስ ቴክኖሎጅዎች በመታገዝ እንዲያመርቱ በማድረግ የምገባ መርሃ-ግብሩን እንዲያግዙና ለተማሪዎችም የተግባር መማሪያ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡

## 1.6. የፖሊሲ ማዕቀፍ


የበለፀገች ኢትዮጵያን ማየት
ለዘላቂ ልማት ግቦች መሳካት አስተዋፅዖ ማበርከት
የ 10 ዓመት የብልጽግና ጉዞ ዕቅድ መሰካት
ክትትልና ድጋፍ
ትምህርት
ጤና
ግብርና
የአካባቢ ግብርና እና ኢንዱስትሪ ልማት
ገቢና የስራ እድል መፍጠር
ትምህርትና የሰው ሃብት ልማት
ጤናና ስርአተ ምግብ መሻሻል
ማህበራዊ ጥበቃና ደህንነት መረጋገጥ
የስርአተ ጾታ እኩልነት መፈጠር
አገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር
ሀገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ

# ክፍል ሁለት

# 2. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማዎችና ምሰሶዎች (Pillars)

ኢትዮጵያ ዜጎችን መሰረት ያደረገ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት የጀመረችውን የብልፅግና ጉዞ ለማስቀጠል በቁርጠኝነት እየሰራች ትገኛለች፡፡ ከዚህ አንፃር የትምህርት ተሳትፎንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አንዱ ዜጎችን መሰረት ያደረገ ሁለንተናዊ እድገት ለማምጣት የሚያግዝ ቁልፍ መንገድ ነው፡፡ የትምህርት ተሳትፎንና ውጤታማነትን ለማምጣት በየትምህርት ቤቶቹ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን መተግበር ደግሞ ለነገ የማይባል ወሳኝ የመጪው ትውልድ ግንባታ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግሥት የህፃናትን የመማር መብት ለማረጋገጥ፣ ሙሉ አቅማቸውን እንዲያዳብሩ እና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ቀርጾ መንቀሳቀስ እንደሚገባ በመታመኑ ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ ፖሊሲ ዋና ተልዕኮም ከሚመለከታቸው ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ፣ ከማህበረሰብ ፣ ከልማት አጋሮች እና ከሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሁሉም የቅድመ አንደኛና እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጆች ለአካላዊ እና አዕምሮአዊ እድገታቸው የሚያስፈልግና የተመጣጠነ ምግብ እዲያገኙ በማድረግ የትምህርት ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ ነው፡፡

## 2.1. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማዎች እና የተፈጻሚነት ወሰን

### 2.1.1. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ራዕይ

በ2023 ዓ.ም ሁሉም በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የሥርዓተ-ምግብ ዋስትናቸው የተረጋገጠ፣ ጤናማ፣ በትምህርታቸው ውጤታማና ብቁ ዜጎች ሆነው ማየት፡፡

### 2.1.2. የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ተልዕኮ

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን ደረጃ በደረጃ በመተግበር ቀጥተኛና ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ሴክተሮች ቅንጅታዊ አሰራርን በመዘርጋት በቅድመ አንደኛና መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡

### 2.1.3. ግብ

የትምህርት ቤት ምገባን በሁሉም የቅድመ አንደኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመተግበር የህፃናትን የትምህርት፣ የጤና እና የአመጋገብ ሁኔታን በማሻሻል በሀገራዊ ደረጃ ለታለሙ የብልጽግና ግቦች መሳካት አስተዋፅኦ ማድረግ ነው።

### 2.1.4. የፖሊሲው ዋና ዓላማ

የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲው ዋና ዓላማ ለሁሉም የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በየዕለቱ በንጥረ ምግብ የበለፀገ ምግብ በማቅረብ የትምህርት ብክነትን በመቀነስ የተማሪዎችን ውጤታማነት ማሻሻል፣ ጤናማና አምራች ዜጎችን መፍጠር ነው።

### 2.1.5. ዝርዝር ዓላማዎች

የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ዝርዝር ዓላማዎች፦

i. የቅድመ አንደኛና መጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ እና ውጤታማነትን በማረጋገጥ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል፣
ii. በምገባ መርሃ ግብሩ የታቀፉ ተማሪዎች በቂ፣ ደህንነቱ የተረጋገጠ እና የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በማድረግ የአጭር ጊዜ ረሃብን በማስወገድ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ ማስቻል፣
iii. በወንዶችና ሴት ተማሪዎች መካከል ያለውን ፆታዊ ምጥጥንን ማሻሻል፤
iv. የትምህርት ቤት ምገባን በአካባቢው ከሚገኙ አርሶ አደሮች ጋር በማስተሳሰር ለሴቶችና ወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር፣ የአርሶ አደሩን ገቢና ምርታማነትን ማሳደግ
v. ተማሪዎች በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ጊዜ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት መስጠት

## 2.2. የፖሊሲው ወሰን

ይህ ፖሊሲ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ በመባል ይጠራል። ፖሊሲው የትምህርት ቤት ምገባ በአለም አቀፍ ደረጃ ዘርፈ ብዙ እውቅና ባተረፈባቸው የትምህርት፣ ጤናና ስርዐተ ምግብ፣ ማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ፣ ግብርናና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ላይ ያተኮረ ነው። በተጨማሪም በዘላቂ ፋይናንስ ምንጭና ቁልፍ አደረጃጀቶች ላይም ያተኩራል።

የዚህ ፖሊሲ ወሰንም በሀገር አቀፍ ደረጃ በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር እና ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው የመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ በክልል መንግስታት እንዲሁም የትምህርት ቤት ምገባ አገልገሎት በሚደግፉ አጋር ድርጅቶችና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ዘንድ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ፖሊሲው ለአስር ዓመት (ከ2013-2023 ዓ.ም) ታሳቢ የተደረገ ሲሆን ከዘላቂ ልማት ግቦች፣ ከአስር አመቱ የብልፅግና ጉዞ እቅድ፣ ከትምህርት ፍኖተ ካርታ፣ ከምግብና ስርአተ ምግብ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም ሌሎች ሀገራዊ የስምምነት ሰነዶች ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ ፖሊሲው በ2018 ዓ.ም የሚከለስ ሲሆን ለትግበራ እንዲመች የተለያዩ መመሪያዎች የሚዘጋጁለት ይሆናል፡፡

## 2.3. የፖሊሲው ተጠቃሚዎች

የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ለትምህርት የተመዘገቡ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ (1-8ኛ ክፍል) ተማሪዎችን ያቀፈ ይሆናል፡፡ አተገባበሩም ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን አካባቢዎች ቅድሚያ በመስጠት ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ ይሆናል፡፡ የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ምርትና ምርታማነት እንዲሁም በምገባ እዝ ሰንሰለት ውስጥ የሚያልፉ ገበሬዎችን፣ ዩኒየኖችን፣ ፋብሪካዎችን፣ የህብረተሰብ ክፍሎችን፣ ወላጆች፣ እናቶች፣ ወጣቶችና ሌሎችም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የዚህ ፖሊሲ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 2.4. የፖሊሲው እሴቶችና መርሆዎች

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ፖሊሲ የሚከተሉትን ዕሴቶችና መርሆዎችን ታሳቢ በማድረግ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

1. **የጋራ ኃላፊነት፡-** ባለድርሻ አካላትና የሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በሁሉም ደረጃዎች የጋራ ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤
2. **ግልፅነትና ተጠያቂነት፡-** ሁሉም ባለድርሻዎች ለስራዎች ቁርጠኛ በመሆንና ኃላፊነት በመውሰድ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት በተሞላበት አግባብ መንቀሳቀስና በፕሮግራሙ ዙሪያ ግብረ-መልሶችንና ተፈላጊ መረጃዎችን ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤
3. **ልጅ ተኮር ማድረግ፡-** ለልጆች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ቅድሚያ መስጠት፤ ህፃናት በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለጤንነታቸው ተስማሚ፣ በንጥረ ምግብ ይዘቱ የተሟላና በቂ

ምግብ በማግኘት ከረሃብ ነፃ ሆኖ የመማር ህገ-መንግስታዊ መብታቸው መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል፣

4. **በባለሙያና በዕውቀት መምራት፡-** ፕሮግራሙ ዕውቀት፤ ሙያና ልምድ ባላቸው አካላት እንዲመራ ይደረጋል፤

5. **ቅንጅታዊነት፡-** ሁሉም ባለድርሻ አካላት በፖሊሲው ትግበራ ላይ በተቀናጀ መልኩ እንዲሳተፉ ይደረጋል፣

6. **ፍትሃዊነት፤ እኩልነትና ማህበራዊ ዖታ መላሽነት፡-** ፕሮግራሙ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ህፃናትን፤ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም በአደጋ ተጎጂ የህብረተሰብ ክፍሎችን በፍትሃዊነት ተጠቃሚ ያደርጋል፤

7. **ፈጠራ፣ ተለማጭነትና ተላማጅነት**፡- በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚገኙ ሀገር በቀል ዕውቀቶች፣ ልምዶችና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን በመቀመርና የህብረተሰቡን አመጋገብ ስርዓት ታሳቢ በማድረግ ዘላቂ የምግብ ሰንሰለት የሚያበረታታ ይሆናል፤

8. **ባህልና ሃይማኖትን መጠበቅ፡-** ፕሮግራሙ የህፃናቱን ባህልና ሃይማኖትን በማክበር ትክክለኛ የምግብ ምርጫ እንዲኖራቸው የማድረግ ማዕቀፍ የሚያስቀምጥ ይሆናል፤

9. **ህብረተሰብ አሳታፊ**፡- ህብረተሰቡ በመርሃ-ግብሩ እቅድ ዝግጅት፣አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ ላይ በባለቤትነት የሚሳተፍበትን አሰራር የሚዘረጋ ይሆናል፡፡

## 2.5. የፖሊሲው መሰረታዊ ምሰሶዎች/Policy Pillars)

I. ለሀገር በቀል ምርቶች ትኩረት በመስጠት ሁሉም የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ የተመጣጠነና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

II. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አደረጃጀት ይፈጠራል፣ የአቅም ግንባታና ግንዛቤ ማሳደጊያ ስራ ይሰራል

III. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የዘላቂ የበጀት ምንጭን እንዲኖረው ይደረጋል፣

IV. ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋት ለምገባው ትግበራ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣

# ክፍል ሦስት

# 3. የፖሊሲ ጉዳዮች፣ አቅጣጫዎችና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ ዓላማዎችን ለማስተግበር የሚከተሉት የፖሊሲ ጉዳዮች፣ ስልቶችና ስትራቴጂዊ ማስፈፀሚያዎች ተዘጋጅተዋል። በዚህም መሰረት የሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲ አምስት የፖሊሲ ጉዳዮችና የትኩረት መስኮች ማለትም ትምህርት፣ ንጥረ ምግብና ጤና፣ ማህበራዊ ጥበቃ እና የፆታ እኩልነት፣ ግብርና/አካባቢያዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ አመራርነት እና የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር በመዘርጋትና ቋሚ የፋይናንስ ምንጭ በመፍጠር ዘላቂነቱ የተረጋገጠ የሃገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ እንዲተገበር ማድረግ ነው።

በዚህም ውጤታማና ዘላቂ የትምህርት ቤት መርሃ-ግብርን ለመተግበር እንዲቻል በዚህ ሰነድ ውስጥ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች/ምሰሶዎች እና ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች በሚከተለው መልኩ ተብራርተው ተቀምጠዋል።

## 3.1. የፖሊሲ ጉዳይ አንድ ፡- ለሀገር በቀል ምርቶች ትኩረት በመስጠት ሁሉም የቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ የተመጣጠነና ደህንነቱ የተጠበቀ ምግብ ማግኘት አለባቸው።

የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የሰው ሀብት ልማትን ለማምጣት እና በሀገር ደረጃ ተመጣጣኝ እድገት እንዲሰፍን ለማድረግ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር አገልግሎት በሁሉም ቅድመ አንደኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወጥ የሆነ አሰራር ተዘርግቶለት መተግበር አለበት። ለዚህም ይረዳ ዘንደ የሚከተሉት ስልቶች ተቀምጠዋል።

### ስልት አንድ፡- ለትም/ቤት ምገባ አገልግሎት የሚዉሉ የምርት ግብአቶች በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘላቂነትና በበቂ ሁኔታ እንዲመረቱ ማድረግ፣

#### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. ሰፋፊ የእርሻ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም፣ የትምህርት ቤት እርሻ ቦታዎች እና በአካባቢዉ የሚገኙ ማሳዎችን በዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ በመጠቀም ለት/ቤቶች የምገባ አገልግሎት እንዲውሉ ይደረጋል፣
2. የአካባቢው አስተዳዳር እና ማህበረሰቡ ለትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት የሚውሉ የእርሻ ቦታዎች ይዘጋጃሉ፣
3. ለሰብል ምርት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ወይም ለእንስሳት እርባታ የሚያገለግሉ የመሬት ይዞታ ያላቸው ትምህርት ቤቶች በዘመናዊ የአመራረት ዘዴዎች በመጠቀም ለትምህርት ቤት የምገባ አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶች እንዲያመርቱ ይደረጋል፡፡
4. በተለያዩ ቦታዎች አዋጪ የሆኑ አነስተኛና መካከለኛ የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እንዲቋቋሙ ማድረግ
5. የተደራጁ እናቶች፣ ወጣቶችና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የምግብ ግብአቶችን ማምረትና ማቅረብ እንዲችሉ ማድረግ፣

## ስልት ሁለት፡- ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባን በአካባቢው ከሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ጋር ማስተሳሰር፡-

### ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

1. በንጥረ ምግብ ይዘታቸው የዳበሩ ምርቶችን በአካባቢው ከሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች እንዲመረቱ በማድረግና የገበያ ትስስር በመፍጠር የትምህርት ቤት ምገባን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣
2. የአካባቢው አርሶ/ አርብቶ አደሮች ወተትና እንቁላል በስፋት እንዲያመርቱና ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ገብር እንዲያቀርቡ ማስቻል፣
3. በአርሶ/አርብቶ አደሩ ግብርና ምርቶች እና የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች መካከል ጠንካራ ትስስር መፍጠር
4. በአካባቢው የሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደር ህብረት ሥራ ዩኒየኖች አማካይነት ጥራቱን የጠበቀና ለምገባው በቂ የሆነ ምርት እንዲያቀርቡ በማስቻል የአርሶ/አርብቶ አደሩን የገቢ አቅም ማሳደግ፣

## ስልት ሶስት፡- ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን ማሟላት፡-

ለትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት የሚውሉ ንፁህ ውሃ፣ አስተማማኝነታቸው የተረጋገጡ የምግብ ግብዓት ማስቀመጫ መጋዘኖች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ ማብሰያ ቤቶች፣ በቂ የልጆች የመመገቢያ ቦታዎች፣ ደረጃቸውን የጠበቁ መታጠቢያና መፀዳጃ ቤቶች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብር የሚያገለግሉ ግንባታዎች አዲስ ለሚቋቋሙ ትምህርት ቤቶችም እንደ መስፈርትነት ያገለግላሉ፡፡

ማብሰያ ቤቶች እንደ ሞዴል የማህበረሰብ የሽግግር ማእከሎች ያገለግላሉ፡፡ የማብሰያ ቤቶች የምግብ ደህንነትንና ጥራትን፣ የልጆች እኩልነትን፣ የአመጋገብ ስርዓትንና በአካባቢ የምግብ ግብዓቶች እንዴት በንጥረ ነገሮች የበለፀጉ ጠቃሚ ምግቦችን ማብሰል እንደሚቻል ማህበረሰቡን የምናስተምርባቸው፣ የልምድ ልውውጥ የሚደረግባቸው ሞዴል የማህበረሰብ ስልጠናና የሽግግር ማዕላት ይሆናሉ፡፡

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. በትምህርት ቤቶች ውስጥ የምገባ መሰረተ ልማቶች ደረጃቸውን የጠበቁ (ማብሰያ፣ መመገቢያ አዳራሽ፣ የምግብ ማከማቻ መጋዘን) ግንባታ በመደበኛው የትምህርት ቤት ስታንዳርድ ውስጥ ተካቶ እንዲሰራ ማድረግ፣
2. ደረጃቸውን የጠበቁ የምግብ ማብሰያና መመገቢያ ቁሳቁስ ማሟላት፣
3. የንፁህ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ መታጠቢያና መጸዳጃ አገልግሎትን ማሟላት፣ ንጹህና ጤናማ አካባቢን ለመፍጠር የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃን ማሟላት፣
4. የመመገቢያ አካባቢን ጽዱ ውብና ማራኪ እንዲሆን ማድረግ፣
5. ለምገባ አገልግሎት የሚውሉ ዘመናዊና ባህላዊ ጊዜን፣ጉልበትንና ኃይል ቆጣቢ እንዲሁም ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የምግብ አዘገጃጀት አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአካባቢ ብክለትንና መራቆትን መከላከል ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት

## ስልት አራት፡- የሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትና የምግብ ዋስትና ላልተረጋገጠላቸው ማህበረሰቦች ቅድሚያ በመስጠት መተግበር፣

### ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

1. ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሀገራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የዳሰሳ ጥናቶችን ማከናወን፣
2. ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ውጤታማ የሆነ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ለማከናወን ክልሎች/ ከተማ አስተዳደሮች ስልታዊ እቅድ አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ይደረጋል፣
3. በሀገር ውስጥና በዉጭ የሚመረቱ የምግብ ግብዓቶችን በማቅረብ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ህጻናትና ወጣቶችን የምግብና የሥርዓተ ምግብ ፍልጎትን በተሟላ ሁኔታ ማረጋገጥ፣

## ስልት አምስት: - ትምህርት በአደጋ ጊዜ ለማስቀጠል የሚያስችል የአስቸኳይ ጊዜ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ይዘረጋል፣

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የሚያጋጥሙ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ይስተዋላሉ፡፡ በእነዚህ ክስተቶች ምክንያት ከፍተኛ ተፅዕኖ ከሚደርስባቸው ጉዳዮች አንዱ የትምህርቱ ዘርፍ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህን ተፅዕኖ ለመቋቋምና ትምህርትን በአደጋ ጊዜ ለማስቀጠል የተለያዩ ስልቶችን መጠቀምና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ከታች የተዘረዘሩት ማስፈጸሚያ ስትራጂዎች ተቀምጠዋል፤

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. የትምህርት ቤት ምገባን በማጠናከር በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ በተጎዱ አካባቢዎች ለሚገኙ ተማሪዎች ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት የትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል፤
2. ለአደጋ ጊዜ የማይበገር የትምህርት ሥርዓት ለመዘርጋት ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ፈጣን የሆነ ምላሽ የመስጠት ስርዓት መዘርጋት
3. ለሴት ተማሪዎችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት መስጠት የምገባ መርሃ ግብሩን ማካሄድ፣

## 3.2. የፖሊሲ ጉዳይ ሁለት ፡ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጠራል፣ የአቅም ግንባታና ግንዛቤ ማሳደጊያ ስራ ይከናወናል፤

በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ዙሪያ የሚተገበሩ የአቅም ግንባታ ስራዎች መርሃ-ግብሩን ዘላቂ ለማድረግ፣ በትግበራ ሂደት የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ሊቀርፉ የሚችሉ የብሔራዊ፣ ክልላዊና ተቋማዊ አቅሞችን ለማጠናከር አስፈላጊ ናቸው። ስለሆነም ፖሊሲው በምግብ ጥራትና ማበልፀግ፣ በአያያዝና አጠቃቀም፣ በጥናትና ምርምር በተገኙ ልዶችና ተሞክሮዎች፣ በስልቶችና መርሀ-ግብሮች ቀረፃ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ዙሪያ ትኩረት ይሠጣል።

ፖሊሲው በትግበራ ሂደት በሁሉም ደረጃ የተቋማትን፣ የሰው ሃብትን፣ የግለሰቦችንና የማህበረሰብን አቅም ግንባታ ስራ ትኩረት ይሰጣል። የምገባ መርሃ ገብሩ በትምህርት መዋቅሮች ውስጥ የራሱ አደረጃጀት ተፈጥሮለት በሙያው የሰለጠኑ ባለሙያዎች እንዲመሩት ይደረጋል። በትምህርት ቤት የሚገኙ ወንድና ሴት ተማሪዎች ለሥርዓተ-ምግብ ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ መሆናቸውን በመረዳት ችግሩን ለዘለቄታው እንዲፈታ መፍትሔ በማምጣት ሴቶች ቁልፍ ተዋናይ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለአነስተኛ አርሶ አደሮች፣ የሴቶች አደረጃጀቶችና ማህበራትን፣ የሴቶች የልማት ቡድኖችን አቅም ማጎልበት ትኩረት ይሰጠዋል።

### ስልት አንድ፡- የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብርን ለማስፈፀም የሚያስችል ራሱን የቻለ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠር

#### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ትምህርት ቤት ድረስ በሚኖረው መዋቅር የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን የሚያስፈፅም ራሱን የቻለ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለውን አደረጃጀት ማቋቋም፣
2. ተቋማዊ አደረጃጀቱን በሰለጠነ የሰው ኃይልና ፋይናንስ ማጠናከር፣
3. ተቋሙ የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ-ግብርን እንዲያቅድ፣ እንዲፈፅምና እንዲገመግም የሚያስችለው አቅም መገንባት፣
4. የማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎች ማዘጋጀት፣

## ስልት ሁለት፡- በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ፈጻሚ አካላት የአቅም ግንባታና ግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን ማከናወን

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. የትምህርት ቤት ምገባን ተግባራዊ ለሚያደርጉና በየእርከኑ ለሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች ተከታታይ የሆነና አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት፣
2. በየደረጃው ያሉ አደረጃጀቶችን በቂ በሆነ ቁሳቁስ ማደራጀት
3. በየደረጃው የሚገኝ አመራርና ፈጻሚ አካላት በሀገር ውስጥና በውጭ ጠቃሚ ተሞክሮዎችን እንዲቀስሙ ማድረግ፣
4. የተለያዩ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስልቶችን በመጠቀም ለማህበረሰቡና ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ መፍጠር፣
5. ሀገራዊና አህጉራዊ የትምህርት ቤት ምገባ ቀንን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት፣ በሚዲያና ኮምንኬሽን በማጀብ ማክበር፣በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን፣
6. የትምህርት ቤት ሞዴል ማብሰያ ቤቶች ለአካባቢው ማህበረሰብ የስርዓተ ምግብ ማስተማሪያና የማህበራዊ ሽግግር ማዕከል እንዲሆኑ ማድረግ፣
7. ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በመተባበር የምግብ ዝግጅት ውድድሮችን ማካሄድ፣ በባለሙያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መተግበር፣
8. ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እና ከሌሎች የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር በፕሮግራሙ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣

## 3.3. ፖሊሲ ጉዳይ ሶስት፡- ዘላቂ የበጀት ምንጭን ማረጋገጥ

ሀገር አቀፍ ምገባ መርሃ-ግብርን ዘላቂ ለማድረግ ፈጠራ የታከለበትና አስተማማኝ የሆነ የገንዘብ ምንጭ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለትምህርት ቤት ምገባ መስፋፋት እንደ ዋና ተግዳሮት ከሚታዩ ነገሮች አንዱና ዋነኛው የፋይናንስ ዕጥረት ነው፡ ሆኖም የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በመጪው ዘመን ትውልድ ላይ የሚደረግ አዋጭ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት በመሆኑ ሀገራችን ዛሬ ላይ ካላት ውስን ሀብት በመመደብና ሌሎች የፋይናንስ ማመንጫ ስልቶችን በመጠቀም መርሃ-ግብሩን

ማስፋፋትና ዘላቂ ማድረግ እንዳለባት ይታመናል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉት ስልቶችና ተግባራት ተቀምጠዋል፡፡

## ስልት አንድ፡- የአካባቢዎችን ተጨባጭ ሁኔታን ያገናዘበ የሀብት ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማከናወን፣

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማስፈጸሚያ በሚቀርበው ስልታዊና አመታዊ ዕቅድ መሰረት መንግስት በቋሚነት መደበኛ በጀት እንዲመድብ ማድረግ፣
2. የፋይናንስ ምንጭ ሊሆኑ ከሚችሉ ከግሉ ሴክተር ጋር በትብብር መስራት (Public Private Partnership financing mechanism)
3. ከሰብአዊና ልማት አጋር ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር የገንዘብ ምንጩን ማስፋት፣
4. ወላጆችና ማህበረሰቡ መርሃ-ግብሩን በገንዘብ፣ በጉልበትና በማቴሪያል መደገፍ የሚችሉበትን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፣
5. በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ድርሻ ያላቸው ዋና ዋና የመንግስት ሴክተሮች ወጭ እንዲጋሩ ማድረግ (Co-financing arrangement)
6. ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ከማህበራዊ ሃላፊነት (Social Accountability) ጋር የተያያዙ አዳዲስ የፋይናንስ ማመንጫ ዘዴዎችን (innovative financing mechanisms) መጠቀም (ለትምህርት ቤት ምገባ ታክስ መጣል፣ ከቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች ተጨማሪ ክፍያ መጣል፣ ወ.ዘ.ተ በማድረግ ወደ ሚዘጋጀው ትምህርት ቤት ምገባ ፋይናንስ ቋት እንዲገባ ማድረግ)፣

## 3.4. ፖሊሲ ጉዳይ አራት፡- ቅንጅታዊ የአሰራር ስርአቶችን መዘርጋት፣

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ሴክተር ተሻጋሪ በመሆኑ ውጤታማና ቅንጅታዊ አሰራርን ማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራና በክትትልና ድጋፍ በመሳተፍ የባለቤትነት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ በዚህ ሂደት መንግስት፣ በጎ አድራጊና የልማት አጋር ደርጅቶች፣ የግሉ ሴክተር፣ ህብረተሰቡ፣ የተማሪ ወላጅ ማህበር፣ ወመህ/ወተመህ፣ የትምህርት ቤት አመራሮች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

### ስልት አንድ፡- ከሴክትር መስሪያ ቤቶችና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን መፍጠር፤

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. በሴክተሮችና ባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖረውን ቅንጅታዊ አሰራር የሚያስተባብርና የሚመራ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አስተባባሪ አብይ ኮሚቴ ከፌደራል እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ ማቋቋምና ማጠናከር፣
2. በየደረጃዉ ለሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት፣
3. ኮሚቴው በጋራ እቅድ ዝግጅትና ትግበራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፣

### ስልት ሁለት፡ የማህበረሰብ ተሳትፎን በማሳደግ መርሃ ግብሩን ዉጤታማ ማድረግ ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. ህብረተሰቡ በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በጉልበት ለመርሃ-ግብሩ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ፣
2. በምገባ መርሃ-ግብሩ እቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ሂደት ሙሉ ተሳትፊና ባለቤት እንዲሆን ማስቻል፣

### ስልት ሶስት ፡- አስተማማኝ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት

### ስትራቴጂያዊ ማስፈጸሚያዎች

1. ለፖሊሲው ትግበራ የተጠናከረ፣ ውጤታማና ሁሉን አቀፍ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

2. የክትትልና ድጋፍ ሥርዓቱ የፕሮግራሙን አተገባበርና ውጤታማነት በንፅፅር ሊያሳዩ የሚችሉ መለኪያዎችን/አመላካቾችን ማዘጋጀትና የመርሃ-ግብሩን ውጤታማነትና አፈጻፀም አስቀድሞ በተቀመጡ መለኪያዎች አንፃር በየደረጃው ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፣
3. ለፖሊሲው ትግበራ ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች የመርሃ ግብሩን አፈጻጸም በጋራ ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፣
4. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የመረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል። የመረጃ ልውውጥ ስርዓቱን ለማጠናከር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረግ፣
5. የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በአመታዊ የትምህርት መረጃ ስርዓት ውስጥ ማካተት፣ መተንተን እና ለውሳኔ መጠቀም፣

# ክፍል አራት

## 4. የምግብ ይዘትና ግዢ ስርዓት

### 4.1. የምግብ ይዘት

በምገባ መርሃ-ግብሩ ለተማሪዎች የሚቀርቡ ምግቦች የየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ተደርጎ በጤናና ስርአተ ምግብ ባለሙያዎች የሚዘጋጅ ይሆናል። በዚሁ መሰረት ለተማሪዎች የሚቀርቡ ምግቦች ለህጻናቱ በንጥረ ምግብ ይዘታቸው የተሟሉ፣ ደህንነታቸውና ንፅህናቸው የተጠበቀ፣ በአካባቢው ተመርተው ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚገኙ ሀገር በቀል ዕውቀቶች፣ ልምዶችና ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችን በመቀመርና የህብረተሰቡን አመጋገብ ስርዓት ግምት ውስጥ በማስገባት በስርዓተ ምግብ ጥናት ላይ የተመሰረተ የትምህርት ቤት ምገባ የምግብ ይዘት ይዘጋጃል።

ለአንድ ጊዜ የትምህርት ቤት ምገባ ለአንድ ተማሪ በቀን ከ120-150 ግራም ምግብ የሚያስፈልገው ሲሆን ይህም ከተለያዩ የእህል አይነቶች፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች (የምግብ ዘይትና በአዮዲን የበለፀገ ጨው)፣ በየአካባቢዉ የሚገኙ የስራ ስርና ሌሎች ተክሎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬዎች፣ የእንስሳት ተዋፅኦዎች ሌሎችንም የሚያካትት ይሆናል። ይህም ለልጆች በቀን ከሚያስፈልጋቸው ከ1850-2100 ኪሎ ካሎሪ ውስጥ 1/3ተኛ ያህሉን (የዕለት ፍጆታው ከ616-700 ኪሎ ካሎሪ እና ከ28-36ግ ፕሮቲን) የያዘ ይሆናል።

ለትምህርት ቤት መርሃ ግብር የሚዘጋጀው የምግብ ዝርዝር (ሜኑ) የአካባቢውን አመጋገብ ባህል፣ የተማሪዎች ፍላጎትና አጠቃላይ የምግብ አቅርቦት መሰረት በማድረግ በዞን ወይንም በወረዳ ደረጃ በሥነ-ምግብ ባለሙያዎች የሚዘጋጅ ይሆናል።

### 4.2. የግዥ ስርአት

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ለምገባ የሚያገለግሉ አስፈላጊ የምርት ግብአቶችን (food commodities) ያልተማከለ የግዥ ስርአትን በመከተል ለትምህርት ቤቱ ቅርብ ከሆኑ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮች፣ እንዲሁም ለዚህ ተብለው ከተለዩ ሰፋፊ እርሻዎች የሚያገኝ ሲሆን እንደ ጨውና ዘይት የመሳሰሉት የፋብሪካ ውጤቶችም በሀገር ውስጥ ካሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲገዙ በማድረግ የምገባ

መርሃ-ግብሩ ይተገበራል፡፡ ምግብ አጠር በሆኑ ክልሎች ወይም አካባቢዎች፣ ከአቅም ውስንነት እና ከመሰረተ ልማት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ለሚከሰት ችግር በክልሉ አማካኝነት በተማከለ ግዥ ሊፈጸም ይችላል፡፡ የምግብ ግብዓቶችን በአካባቢው የሚገኙና ሊገኙ የማይችሉትን በመለየት በማዕከልና ባልተማከለ መልኩ ግዥ ሊፈጸም ይችላል፡፡

ለትምህርት ቤት ምገባ የሚውለው የምግብ ግብዓት በአርሶና አርብቶ አደር ህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት፣ በነጋዴዎች፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፤ ቡድኖች በግዢ ሥርዓት አቅራቢዎች ይሆናሉ፡፡

ለትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት ተዘጋጅቶ/ተደራጅቶ ትምህርት ቤት የደረሰን ምግብ ከትምህርት ቤቱ ወይም ከሌላ አካል ጋር በሚደረግ ስምምነት በትምህርት ቤት ምግብ አብሳዮች በሙሉም ሆነ በከፊል በስሎ ለተማሪዎች ይቀርባል፡፡

ትምህርት በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ክስተት ምክንያት አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በመንግስት ግዥም ይሁን በአጋር ድርጅቶች ድጋፍ በቀጥታ ከውጭ ሊገባ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ለስደተኞች በተሟላ መልኩ እንዲዳረስ ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የምገባ መርሃ-ግበሩ አካታች እንዲሆን ጥረት ይደረጋል፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብሩ አጠቃላይ ትግበራና የግዥ ሂደት ለዚህ ዓላማ በሚዘጋጀው የማስፈጸሚያ መመሪያ መሰረት የሚመራ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ የግብአት ፍሰትን የሚያሳየው የትግበራ ሞዴል ከዚህ በታች በተመከተው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## የግዥ ትግበራ ሞዴሎች ማጠቃለያ

| አይነት | ምርት | አቅራቢዎች | ግዥ ሂደት |
|---|---|---|---|
| ከእርሻ ወደ ትም/ቤቶች ማዕድ ቤት(Farm to School) | አነስተኛ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደር/የትም/እርሻዎች/የተደራጁ ቡድኖች/እናቶች/መሰረታዊ ማህበራት/ማህበረሰቡ | | ትም/ቤት(የተደራጁ እናቶች) |
| ያልተማከለ ዘዴ( Decentralized) | አነስተኛ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደር/አምራቾች | ነጋዴዎች<br>ዩኒየኖች/መሰረታዊ ማህበራት | ትም/ቤቶች/ዞኖች/ወረዳዎች/ከተማ አስተዳዳሮች/የተደረጁ ቡድኖች |
| በከፊል ያልተማከለ ዘዴ(Semi-Decentralized) | አነስተኛ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደር/አምራቾች/ሰፋፊ እርሻዎችና የእንስሳት እርባታ ማዕከላት | ነጋዴዎች<br>ዩኒየኖች/መሰረታዊ ማህበራት | ትም/ቤቶች/ዞኖች/ወረዳዎች/ከተማ አስተዳዳሮች/የተደረጁ ቡድኖች<br>የፌደራል/የክልል መንግስት |
| የተማከለ ዘዴ(Centralized) | አነስተኛ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደር/አምራቾች/ሰፋፊ እርሻዎችና የእንስሳት እርባታ ማዕከላት | ነጋዴዎች<br>ዩኒየኖች/መሰረታዊ ማህበራት | የፌደራል/የክልል መንግስት |
| ሶስተኛ ወገን(Outsourced Modality) | አነስተኛ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደር | ነጋዴዎች<br>ዩኒየኖች/መሰረታዊ ማህበራት | አቅራቢዎች/Caterers |

# ክፍል አምስት

## 5. የፖሊሲና ስትራቴጂው ፈጻሚ ተቋማትና የባለድርሻ አካላት ሚና

ከላይ በፖሊሲና ስትራቴጂ ዋና ዋና ጉዳዮች እንደተገለጸው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ- ግብር ትግበራ የአንድ ሴክተር ብቻ ሳይሆን የብዙ ሴክተሮችን ልምዶች ያገናዘበና ውጤታማ ሊሆን በሚችል አግባብ ተቀናጅተው በአንድ የፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ እንዲሁም ፕሮግራም ውስጥ ተቀርፀውና ተቀናጅተው በተጠያቂነት ለአንድ ግብ መስራት የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ በየደረጃው ያለው የትምህርት መዋቅር ማለትም የፌደራል፣ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የትምህርት ቤት አመራር ኃላፊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት የጎደለው በመሆኑ በየጊዜው የሚወጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ ስትራቴጂክ ዕቅዶችና መመሪያዎች ሙሉ በሙሉ ላለመተግበራቸው እንደዋና ምክንያት ሲጠቀስ ቆይቷል፡፡

ከዚህ አንፃር ለፖሊሲው ትግበራ ሂደት የፌደራልና የክልል መንግስታት ለመርሃ-ግብሩ አጠቃላይ አመራር መስጠት፣ ማስተባበር፣ መተግበር፣ ሀብት ማፈላለግ፣ በጀት መመደብና የመርሃ-ግብሩን አፈጻጸም መከታተልና መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲሁም እንደ የክልሎች ሁኔታ የዞንና የወረዳ አስተዳደሮች ተመሳሳይ ሥራ ድርሻና ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የልማት አጋሮች የቴክኒክ፣ የፋይናንስ፣ ቀጥታ ፕሮግራም ትግበራና አቅም ግንባታ ድጋፍ ለመንግስት የሚሰጡ ይሆናል፡፡ የግሉ ሴክተር ደግሞ የመንግስትን ጥረት በፋይናንስ፣ ምግብን በማደራጀትና ለትምህርት ቤቶች በማቅረብና መርሃ-ግብሩን ከአምራች አርሶ አደሮች በማገናኘትና የአካባቢውን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማነቃቃት እገዛ ያደርጋሉ፡፡ በመጨረሻም የአካባቢው ህብረተሰብ መርሃ-ግብሩን በባለቤትነት ዕለት በዕለት እየተከታተለ ይተገብራል፣ በገንዘብ፣ማቴሪያልና ጉልበት ይደግፋል፣ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

በመሆኑም የፌደራል፣ የክልል መንግስታት ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚመለከታቸው ቢሮዎችና አጋር ድርጅቶችን በማስተባበርና በመምራት የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ሲሆን የፈፃሚ ቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተግባርና ሀላፊነት እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## 5.1. የትምህርት ሴክተር ተግባርና ኃላፊነት

| አስተዳደር እርከን | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| የትምህርት ሚኒስቴር | ➢ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ የትምህርት ቤት ምገባ አደረጃጀት እንዲፈጠር ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣<br>➢ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ያከናውናል፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በኮሚኒኬሽን እና በህዝብ ግንኙነት ሥራዎች በማጀብ ትግባራዊ ያደርጋል፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ ፖሊሲን፣ ስትራቴጂንና የተለያዩ መመሪያዎችን ማውጣት እና እንዲተገበሩ ማድረግ<br>➢ በምገባ መርሃ-ግብር ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምርን ማካሄድ<br>➢ ከሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ዘላቂ የሆነ ምገባ መርሃ-ግብሩን ለማስፈፀም የሚያስችል አጋርነት ይመሰርታል፣<br>➢ ከሴክተር ሚኒስቴር መስሪያ እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የትምህርት ምገባ መርሃ-ግብርን ማቀድ፣ መተግበር እና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የጥራት ስታንዳርድን ማውጣት እና ለክልል ቢሮዎቸ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማስፈፀሚያ በጀት በበጀት ርዕስ እንዲካተትና በበጀት እንዲደገፍ ማድረግ<br>➢ የተለያዩ የሀብት አሰባሰብ ዘዴዎችን በመንደፍ ሀብት ማሰባሰብ እና ለትምህርት ቢሮዎች የድጎማ በጀት መስጠት<br>➢ አገር አቀፍ ዘመናዊ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓትን መዘርጋትና ወቅቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ<br>➢ አለም አቀፍና አገራዊ የምክክርና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችን በመቀመር በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ<br>➢ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ላይ ጥናቶችን፣ አውደ ርዕዮችን፣ ሴሚናሮችን ያደራጃል፣<br>➢ ለሰው ሰራሽና ለተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቅድመ ዳሰሳ ማካሄድ፣<br>➢ የልማት አጋር ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ፍትሃዊ |

| አስተዳደር እርከን | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ስርጭት እንዲኖር ይሰራል፣<br>➢ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፎረም ይመሰርታል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ |
| **የክልል / ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች** | ➢ ከክልል ትምህርት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤቶች ያለውን አደረጃጀት መዘርጋት፣<br>➢ የትምህርት ቤት የምገባ መርሃ-ግብር በክልሉ ስልታዊና አመታዊ እቅድ ውስጥ በመካተት እየተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ<br>➢ የተለያዩ የሀብት አሰባሰብ ዘዴዎችን በመንደፍ ሀብት ማሰባሰብ<br>➢ በክልሉ መንግስት መደበኛ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ማስፈፀሚያ በጀት እንዲመደብ ማድረግ<br>➢ ከተለያዩ የግል ባለሃብቶችና ግለሰቦች የሚገኝ ሀብት በአንድ ቋት ገብቶ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማስፈፀሚያ እንዲውል ማድረግ፣<br>➢ የሚፈፀመው የትምህርት ምገባ መርሃ-ግብር በወጣው ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ<br>➢ ውጤታማ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር እንዲተገበር ለዞኖችና ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤቶች የቴክኒክ፣ የአቅም ግንባታና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ<br>➢ ከሴክተር ቢሮዎችና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ዘላቂ የሆነ ምገባ መርሃግብሩን ለማስፈፀም የሚያስችል አጋርነት በመመስረት<br>➢ ከሴክተር ቢሮዎችና አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የትምህርት ምገባ ፕሮግራምን ማቀድ፣ መተግበር እና ክትልና ግምገማ ማድረግ<br>➢ ክልላዊ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን ማዘጋጀት እና ተደራሽ ማድረግ<br>➢ የምክክርና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችን በመቀመር በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ<br>➢ ሪፖርትና መረጃ ለሚኒስቴር መ/ቤቱና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣<br>➢ በክልሉ ውስጥ ለሰው ሰራሽና ለተፈጥሮ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቅድመ ዳሰሳ ማካሄድ፣<br>➢ የምግብ ጥረት ያለባቸውን አካባቢዎች የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ስኬት ትርፍ አምራች ከሆኑ አካባቢዎች የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣<br>➢ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የልማት አጋር ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ፍትሃዊ ስርጭት እንዲኖር ይሰራል፣<br>➢ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ |

| አስተዳደር እርከን | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ያልሆኑ ድርጅቶች ፎረም ይመሰርታል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ |
| **የዞን/የከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያዎች** | ➢ የትምህርት ቤት ምገባ አደረጃጀት መፈጠሩንና በሰው ፣ በፋይናንስ እና በቁሳቁስ መደራጀቱን ያረጋግጣል፣<br>➢ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ምገባ መርሃ-ግብርን ማቀድ፣ መተግበር እና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>➢ ከወረዳዎች/ክፍለ ከተሞች የተላከውን ሪፖርት አጠናክሮ ለክልሎች መላክ<br>➢ ከሴክተር መምሪያዎችና አጋር አካላት ጋር ዘላቂ የሆነ አጋርነት መመስረት<br>➢ የተለያዩ የሀብት አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ከተለያዩ የሀብት ምንጮች ሀብት ማሰባሰብ<br>➢ ውጤታማ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር እንዲተገበር ለወረዳ ትምህርት ጽህፈትቤቶች የቴክኒክ፣ የአቅም ግንባታና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ<br>➢ የምክክርና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማዘጋጀት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎችን በመቀመር በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ |
| **ወረዳ/ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች** | ➢ አደረጃጀት መፈጠሩንና በሰው ፣ በፋይናንስ እና በቁሳቁስ መደራጀቱን ያረጋግጣል፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ በዓመታዊ እቅድ መካተቱንና በበጀት መደገፉን ያረጋግጣል፣<br>➢ ለምገባ መርሃ-ግብር የሚሆን ሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ ማስተዳደር<br>➢ ትምህርት ቤቶች ውጤታማ የሆነ የትምህርት ምገባ መርሃ-ግብር እንዲያካሂዱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>➢ ወርሃዊና የሩብ አመት የትምህርት ቤት የምገባ መርሃ-ግብር አፈፃፀም ሪፖርትን ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ<br>➢ የአቅም ግንባታ እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለትምህርት ቤቶች እና ለሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ይሰጣል፣<br>➢ በትምህርት ቤቶች የሚካሄደው ምገባ ስታንዳርዱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣<br>➢ ከሀገራዊ እና ክልላዊ የምግብ ዝርዝር በመነሳት የትምህርት ቤት ምገባ ሜኑ ከባለሙያዎች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣<br>➢ በወረዳ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ደርጅቶችን፣ ባለሃብቶችን ለምገባው ተግባር ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣ |

| አስተዳደር እርከን | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | የጋራ እቅድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል ፣ ይከታተላል፣<br>➢ የወላጆችና የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲጠናከር አበክሮ ይሰራል፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር በትምህርት ውጤት፣ በጤናና ስርዓተ ምግብ፣ እንዲሁም በአካባቢው አርሶ/ አርብቶ አደሮች የገቢ ሁኔታ ላይ የመጣውን ለውጥ ያጠናል፣ የማሻሻያ ሃሳብ በማቅረብ ይተግብራል፣ |
| **የትምህርት ቤቶች** | ➢ ከማህበረሰብ ጋር በመተባባር የትምህርት ምገባ መርሃ ግብር የፍላጎት ትንተናዎችን ማካሄድ<br>➢ በተማሪዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማቀድ፣ መተግበር<br>➢ የተለያዩ የሀብት አሰባሰብ ዘዴዎችን በመጠቀም ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ሀብት ማሰባሰብ፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን ክትትልና ግምገማ ማድረግ<br>➢ የትምህርት ቤት የጓሮ አትክልት ልማትና የእንስሳት እርባታ ስራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ<br>➢ የወላጆችና የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲጠናከር አበክሮ ይሰራል፣<br>➢ የትምህርት ቤቱን የምገባ ኮሚቴ ያደራጃል፣ እቅድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣ ለወረዳው ሪፖርት ያደርጋል፣<br>➢ በየእለቱ ደህንነቱንና መጠኑን የጠበቀ ምግብ በሜኑ መሰረት እየቀረበ መሆኑን ይከታተላል፣<br>➢ በየእለቱ የሚወጣው ምግብ ከእለቱ የተማሪ አቴንዳንስ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፣<br>➢ የምግብ አከመቻቸት ወይም አያያዝ፣ አበሳሰልና አቅርቦት ስታንዳርዱ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣<br>➢ የፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ የምግብ ማብሰያ፣ በስታንደርዱ መሰረት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣<br>➢ የንጽህ ውሃ፣ መታጠቢያና የመጸዳጃ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣<br>➢ የምግብ አብሳዮች አስፈላጊውን ስልጠና፣ የጤና ምርመራና ክትባት መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፣ |

| አስተዳደር እርከን | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ➢ የምግብ አብሳዮች አልባሳት፣ የንጽህና ሁኔታ ይከታተላል፣<br>➢ ከአካባቢው የጤና ባለሙያ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣<br>➢ በየእለቱ ከኮሚቴዎቹ የአመጋገብ ሂደት የሚከታተል አባል መመደቡን ያረጋግጣል፣<br>➢ የምግብ አቅርቦት ፍሰት /በቂ ክምችት መኖሩን ያረጋግጣል ጉድለት ካለ አስቀድሞ እንዲቀርብ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፣<br>➢ ታዳሽና ሃይል ቆጣቢ እንዲሁም ለአካባቢው ተስማሚ የማብሰያ ቴክኖሎጅዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣<br>➢ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች ማከሚያ እንክብል አገልግሎት በአመት ሁለት ጊዜ ለተማሪዎች መስጠቱን ይከታተላል፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በትምህርት ውጤት፣ በጤናና ስርዓተ ምግብ፣ እንዲሁም በአካባቢው አርሶ/ አርብቶ አደሮች የገቢ ሁኔታ ላይ የመጠውን ለውጥ ያጠናል፣ የማሻሻያ ሃሳብ በማቅረብ ይተግብራል፣ |

## 5.2. የሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| የጤና ሚኒስቴር | ➢ የትምህርት ቤት ምገባን በሚኒስቴሩ ስትራቴጅክና አመታዊ እቅድ ማካተት<br>➢ በትምህርት ቤቶች አጠቃላይ የሆነ የሥርዓተ-ምግብ፣ የጤና፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና አገልግሎቶቶችን ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት፤ መተግበር<br>➢ የተማሪዎች ምገባ ሃገርበቀል ከሆኑ፣ አካባቢን መሰረት ያደረጉና በንጥረ ምግብ ይዘታቸው ከበለፀጉ ከተለያዩ የምግብ ምድቦች የተሰባጠረ እንዲሆን ማስተዋወቅ<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ ሃገር በቀል ከሆኑ፣ አካባቢን መሰረት ያደረጉና በንጥረ ምግብ ይዘታቸው ከበለፀጉ ከተለያዩ የምግብ ምድቦች የተሰባጠረ የምግብ ዝርዝር (Recipe/Menu) ማዘጋጀት<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት የሚቀርበውን ምግብ ደህንነትና ጥራት ይከታተላል፣ይቆጣጠራል<br>➢ የተማሪዎችን የጤና እና ሥርዓተ ምግብ ሁኔታን በየጊዜው ክትትልና ዳሰሳ ማካሄድ<br>➢ የሥርዓተ ምግብ ምክክር አገልግሎት መስጠት፤ ለአስፈላጊ የጤናና ሥርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች refer ማድረግ |

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ➢ በትምህርት ቤቶች የሥርዓተ-ምግብ እና የጤና ተግባራትን በሚመለከት የተግባቦትና የባህሪ ለውጥ ስራዎን መስራት<br>➢ ሥርዓተ-ምግብና ጤናን በሚመለከት ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ ሥልጠናዎችን መስጠት<br>➢ በትምህርት ቤቶች የሥርዓተ ምግብ ክበቦች እንዲቋቋሙ ማድረግ፤ ተግበራቱን መከታተል መደገፍ<br>➢ የአንጀት ጥገኛ ትላትሎች ማከሚያ እንክብል አገልግሎት በአመት ሁለት ጊዜ ለተማሪዎች መስጠት<br>➢ የምግብ ይዘትና አዘገጃጀት በተመለከተ ለትምህርት ቤት ማህበረሰብ እንዲሁም ለወላጆች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣<br>➢ በትምህርት ቤቶች የግልና የአካባቢ ንፅህና እንዲጠበቅ ተግባራትን ማከናወን፤ አገልግሎቶችን ማቅረብ<br>➢ ለታዳጊ ልጃረዶች የብረትና ፎሌት ማእድናት እንክብሎች በየጊዜው እደላ ማከናወን<br>➢ በትምህርት ቤቶች ምገባ፣ ሥርዓተ-ምግብ፣ የምግብ ደህንነትና ጥራት እንዲሁም የትምህርት ቤት አካባቢና የግል ንፅህናን ተግባራት ላይ ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ<br>➢ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እቅድ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በጀት መያዙን ያረጋግጣል፣ |
| **ውሃ መስኖና ኢነርጅ ሚኒስቴር** | ➢ የትምህርት ቤት ምገባን በሚኒስቴሩ ስትራቴጅክና አመታዊ እቅድ ማካተት<br>➢ ለትምህርት ቤቶች የንፁህ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ማድረግ<br>➢ በየትምህርት ቤቶቹ መፀዳጃ ቤቶችን ግምባታ ደረጃቸውን የጠበቁ (ለሴትና ወንድ ተማሪዎች ጨምሮ) እንዲሆኑ መደገፍና መከታተል፡<br>➢ የእጅ መታጠቢያ መገልገያዎችን መገንባት<br>➢ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃዎችን ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ መከታተልና መደገፍ<br>➢ የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ የውሃ ቧንቧዎችን መጠገንና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ<br>➢ ታዳሽና ሃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን ማምጣት፣ማላመድና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ የሚዘጋጁ የእርሻ ቦታዎች የመስኖ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማገዝ |

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ➢ ክትትልና ግምገማ ተግባራትን ማከናወን<br>➢ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እቅድ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በጀት መያዙን ያረጋግጣል፣ |
| **የግብርና ሚኒስቴር** | ➢ የትምህርት ቤት ምገባን በሚኒስቴሩ ስትራቴጂና አመታዊ እቅዶች ጋር ማስተሳሰር፣ መተግበርና መደገፍ<br>➢ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብሩ በታቀፉ አካባቢዎች ለሚገኙ ባለሙያዎች የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችና ሌሎች አካላት በምርትና ምርታማነት እና በሌሎችም ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ አቅማቸውን መገንባት<br>➢ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በታቀፉ አከባቢዎች ለምገባ የሚውሉ የሰብልና የእንስሳት ተዋፅኦ ምርቶች በበቂ ሁኔታ እንዲመረቱ ማስቻል<br>➢ ለአነስተኛ አርሶ አደሮች የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የግብርና ግብአቶችን ማቅረብና ለምገባው ስራ እንዲውል ማድረግ<br>➢ በትምህርት ቤቶች የሚመረቱ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ስራዎችን መደገፍና ተጠናክረው እንዲሄዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣<br>➢ በትምህርት ቤቶች ሊመረቱ የሚችሉ ሰብሎችን መለየትና ትምህርት ቤቶችን የግብርና ሞዴል በማድረግ ለተማሪዎችና ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>➢ ለትምህርት ቤቶች ሰብል ልማት የሚሆኑ የዘር ብዜትና ጥራት ቁጥጥር ማካሄድ እንዲሁም ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብሩን ከተጠቃሚ አርሶ አደሮች ጋር በማስተዋወቅ ትስስሩን ማጠናከር<br>➢ ለምገባ የሚያስፈልጉ አዳዲስ የምርት አይነቶችን ማላመድ፣ ማስተዋወቅና ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ<br>➢ የውሃ አቅርቦት ባላቸው ትምህርት ቤቶች አካባቢ ጥናት በማካሄድ የመስኖ ስራዎችን በማከናወን ምገባው ዘላቂ እንዲሆን ማስቻል<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ ዘርፍ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መቀመርና ተደራሽ ማድረግ<br>➢ በፕሮግራሙ ትግበራ ዙሪያ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎቸ አጋሮች ጋር በቅንጅት መስራት<br>➢ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እቅድ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በጀት መያዙን ያረጋግጣል፣ |

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| **የገንዘብ ሚኒስቴር** | ➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚያስፈልገውን መደበኛ በጀት በሚቀርበው ዕቅድ መሰረት በወቅቱ እንዲፈቀድ ማድረግ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን ሊያግዙ የሚችሉ ሃገራትና አለማቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ግንዛቤ የመፍጠርና የማግባባት ሥራዎችን በመሥራት ለመርሃ-ግብሩ ተጨማሪ ሃብት ማስገኘት፣<br>➢ ሃገራትና ዓለምአቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር የሁለትዮሽ፤ ሦስትዮሽ ስምምነቶችን በመፈጸም በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አፈፃጸማቸውንም መከታተልና መቆጣጠር፣<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚያገለግሉ ከውጪ በርዳታ፤ በስጦታና በግዥ ለሚቀርቡ ቁሳቁሶች ነፃ የግብርና ቀረጥ ፈቃድና ትብብር ማድረግ፣<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አገልግሎት የሚውሉ ከውጪና ሃገር ውስጥ ለሚገዙ ቁሳቁሶች ልዩ የግዥ መመሪያ በማዘጋጀትና ፈጥነው ሥራ ላይ እንዲውሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ጋር ተያያዥ የውጪ የፋይናንስ ድጋፎች በብሄራዊ ባንክ አካውንት እንዲከፍቱ መፍቀድ፤ አፈፃጸማቸውንም መከታተልና መቆጣጠር፣<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አገልግሎት ከውጪና ከሃገር ውስጥ የተሰበሰቡ የፋይናንስ ድጋፎች በሥራ ላይ መዋላቸውን መከታተልና መቆጣጠር፣<br>➢ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በእቅድ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በጀት መያዙን ያረጋግጣል፣ሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶችም በእቅዳቸው ማካተታቸውን ይከታተላል፣ |
| **ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር** | ➢ ከትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ጋር ተያያዥነት ባላቸው የስራ ዘርፎች ለሚሰማሩና የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን በልዩ ሁኔታ ማበረታታት፣<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚውሉ ምርቶች በጥራት በዓይነትና በመጠን የተሟሉ እንዲሆኑ አቅራቢ ወይም አምራች ኢንደስትሪዎችና ፋብሪካዎችን መደገፍ፤ መከታተልና መቆጣጠር፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን የሚያግዙ የውጪ ቴክናኖጂዎችን ማምጣና ከሃገር ዕውቀት ጋር በማላመድ ምገባ መርሃ-ግሩን ውጤታማ እንዲሆን ማገዝ፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን የሴክተሩ ዕቅድ አካል በማድረግ መደገፍ፣ መከታተልና መቆጣጠር፣<br>➢ በሃገር ውስጥ ተመርተው ወደ ውጪ ከሚላኩት የምግብ ግብዓት መካከል በልዩ ሁኔታ ለትምህርት ቤት ምገባ አገልግሎት እንዲውሉ መፍቀድ፣ |

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ➢ በመንግስት ድጎማ ለማህበረሰቡ ከሚቀርቡ የምግብ ግብዓት መካከል ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር የሚፈለጉ ግብዓትን በልዩ ሁኔታ መፍቀድ፣<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን ለማሳለጥ ለሚፈጠሩ የማህበራት አደረጃጀቶች ዕውቅና መስጠት፣ |
| የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር | ➢ የትምህርት ቤት ምገባን በሚኒስቴሩ ስትራቴጂና እመታዊ እቅዶች ጋር ማስተሳሰር<br>➢ ወደ ትምህርት ቤት የመጡ ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘታቸውን መከታታል፣ መደገፍ እና መቆጣጠር<br>➢ ሴት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ የማበረታቻ ስልቶችን በመንደፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ላይ የምግብ አቅራቢ ሴቶችን በማደራጀት ተገቢውን ድጋፍና ሙያዊ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አፈፃፀምን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ<br>➢ በምገባ መርሃ-ግብር የተገኙ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መቀመርና ተደራሽ ማድረግ<br>➢ በመርሃ-ግብሩ ትግበራ ዙሪያ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋሮች ጋር በቅንጅት መስራት |
| የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ/ዩኒየኖች | ➢ የትምህርት ቤት ምገባን በሴክተሩ ስትራቴጂና አመታዊ እቅዶች ጋር ማስተሳሰር<br>➢ ለተደራጁ የገበሬዎች የህብረት ስራ ዩኒየኖች እና ማህበራት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት<br>➢ ለተደራጁና ለምገባ መርሃ-ግብሩ ምግብ ለሚያቀርቡ ዩኒየኖችና ማህበራት ብድር ማመቻቸት<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ የሚውሉ ግብዓቶችን እንዲያቀርቡ በማድረግ የገበያ ዕድል እና ትስስር መፍጠር<br>➢ ለምገባ መርሃ-ግብሩ የሚቀርቡ ዕህሎች ጥራታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥና ድጋፍ ማድረግ<br>➢ የገበያ ጥናት ማካሄድና ተጨማሪ ማህበራት በስራው ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ<br>➢ የትምርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር ግብኣት አቅራቢ ማህበራትን፣ ቡድኖችን ማደራጀት፣ ማጠናከርና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣<br>➢ በመርሃ-ግብሩ ትግበራ ዙሪያ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች አጋሮች ጋር |

| ሴክተር መ/ቤት | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | በቅንጅት መስራት |
| ብሄራሔዊ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን | ➢ በየደረጃው በሚገኙ ከክልል ትምህርት ቢሮ እስከ ትምህርት ቤቶች ድረስ አደጋን ለመከላከልና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አስፈላጊው መረጃ መሰብሰብና ለትምህርት ሚኒስቴርና ለሌሎች አካላት ተደራሽ ማድረግ፣<br>➢ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ምግብ አጠርና ተጋላጭ ከሆኑ አካባቢዎችን መረጃ መሰብሰብ፤ መተንተንና ተደራሽ ማድረግ፡<br>➢ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ለሚካሄደው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፣<br>➢ በአደጋ ተጋላጭ ክልሎች በተሰበሰበው የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ መሰረት ክልሎችን ሊደግፍ የሚያስችል የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማስፈጸሚያ በጀት መመደብ፣<br>➢ ከልማት አጋር ድርጅቶች፤ ከዓለማቀፋዊና ሃገር በቀል ለጋሽ ድርጅቶች የገንዘብና የቁሳቁስ ክፍተት ሊሞላ የሚያችል ሥራ በማከናወን የሚገኘውን ሃብት ለአስቸኳይ ጊዜ መሥራት፣<br>➢ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የተፈናቀሉ ተማሪዎች የትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ መከታተልና መደገፍ፣<br>➢ የአደጋ መከላከል፤ ፈጣን ምላሽ የመስጠትና አደጋን ያገናዘበ ዕቅድ ዝግጅት አስመልክቶ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት ጉድኝቶች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡፡<br>➢ የአስቸኳይ ጊዜ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም የግብረሰናይ ድርጅቶች እንደ ህይወት አድንና ዘላቂ ተግባር አድርገው እንዲተገብሩት ሃብት እዲያፈላልጉና እንዲመድቡ ያደርጋል፣ |

## 5.3. የክልል መንግስታት

| የአስተዳደር መዋቅር | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| የክልል መስተዳድር | ➢ የክልል መንግስታት በፌደራል ደረጃ የወጡ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች መተግበራቸውን መከታተልና መደገፍ፤<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባን ራሱን ችሎ የሚመራበት መዋቅር መፍጠር፤ ማረጋገጥና ተግባራዊነቱን መከታተል፣<br>➢ የክልል መንግስታት የትምህርት ቤቶችን አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ማስፈጸሚያ የሚቀርብለትን በጀት |

| የአስተዳደር መዋቅር | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | ማጽደቅ፣<br>➢ ከብሄራዊ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚመጣውን የምግብ አጠርና ለአደጋ ተጋላጭ አካባቢዎችን መረጃ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት፣<br>➢ የተለያዩ ሴክተር ቢሮዎችና ሌሎች አጋር አካላት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃለፊነት በአግባቡ መወጣታቸውን መቆጣጠርና መደገፍ፣<br>➢ ከግል ባለሃብቶች፤ ከማህበረሰቡ፤ ከልማት አጋር ድርጅቶች፤ ከዓለማቀፋዊና ሃገር በቀል ለጋሽ ድርጅቶች የምገባ መርሃ-ግብር ክፍተትን ሊሞላ የሚያስችል ሃብት ማፈላለግ አቅጣጫ ይሰጣል፣<br>➢ የምገባ መርሃ-ግብር የታለመለትን ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የድጋፍ የክትትልና ግምገማ በማካሄድ፣አቅጣጫ ይሰጣል፣<br>➢ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባላቸው አካባቢዎች ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ሊያግዝ የሚያስችል መሬት እንዲዘጋጅ አቅጣጫ ይሰጣል፣<br>➢ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር አገልግሎትና ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ለያግዝ የሚያስችሉ አነስተኛና መካከለኛ የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንደስትሪ እንዲከፈቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ |

## 5.4. የአጋር ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ

| የአስተዳደር መዋቅር | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| የአጋር ድርጅቶች | ➢ በፋይናንስ፣ በቁሳቁስ ድጋፍና በቀጥታ ትግበራ በመሳተፍ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን ማገዝ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብርን ሊደግፉ የሚችሉ የአቅም ግንባታና ቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት የመንግስትን ጥረት ማገዝና መደገፍ<br>➢ ለምገባ የሚያግዙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በማምጣት የመንግስትን ጥረቶች ማገዝ<br>➢ በውሃ፣ ሃይጅን ሳኒቴሽንና ስርዓተ-ምግብ ዙሪያ የት/ቤት ምገባ አገልግሎትን መደገፍ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃግብርን ውጤታማነት ሊያሻሽሉ የሚችሉ እንደ ጸረ-ትላትልና ተህዋሲያን ያሉ ድጋፎችን ለትምህርት ቤት ልጆች ማቅረብ<br>➢ አስተማማኝና ዘላቂ የትምህርት ቤት ምገባ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ |

| የአስተዳደር መዋቅር | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|
| | አዳዲስ የአመራረት ስልቶችን በማምጣት የአርሶ አደሩን ምርታማነት ማገዝ<br>➢ ትምህርትን በአደጋ ጊዜ ለማስቀጠል የአስቸኳይ ጊዜ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብርን እንደ ቁልፍ ህይወት አድንና ኑሮ አስቀጣይ የምላሽ ተግባር (Lifesaving and sustaining intervention) በመውሰድ ለሰብአዊ ድጋፍ ሃብት ማፈላለግ፣ ማስተባበርና እገዛ መስጠት |
| **የግሉ ዘርፍ ሚና** | ➢ ባለሀብቶችና በተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብሩን በገንዘብና በቁሳቁስ ማገዝ<br>➢ የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ምግቦችን ለማደራጀት፣ ለማቀነባበርና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን የምገባ መርሃ-ግብሩን ማገዝ<br>➢ የት/ቤት ምገባን ከአምራች አርሶ አደሮች ጋር በማገናኘት የአካባቢውን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማነቃቃት እገዛ ማድረግ<br>➢ በተለያዩ ማምረቻ ዘርፍ የተሰማሩ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ለምገባ መርሃ-ግብር ተሳትፎ በማድረግ ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን (Social Accountability) ይወጣሉ፣ |
| **የወላጆች ህብረት** | ➢ ወላጆችን እና የአካባቢው ማህበረሰብ ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በጉልበት እንዲሁም ወጪ በመጋራት እንዲሳተፉ ያስተባብራል፣<br>➢ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በሚቋቋሙ የትምህርት ቤት ምገባ ኮሚቴዎች ይሰተፋል፣<br>➢ በምገባ መርሃ ግብር እቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ክትትልና ድጋፍ ይሳተፋል፣<br>➢ ወላጆች መር የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር እንዲዘረጋ አስተዋጽኦ ያደርጋል፣ |

# ክፍል ስድስት

## 6. የክትትልና ግምገማ ስርአት

ለፖሊሲው ትግበራ የተጠናከረ፣ ውጤታማና ሁሉን አቀፍ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል። የክትትልና ግምገማ ሥርዓቱ የመርሃ-ግብሩን አተገባበርና ውጤታማነት በንፅፅር ሊያሳዩ የሚችሉ መለኪያዎችን/አመላካቾችን ማዘጋጀትና የኘሮግራሙን ውጤታማነትና አፈጻፀም አስቀድሞ በተቀመጡ መለኪያዎች አንፃር በየደረጃው ይገመገማል።

ለፖሊሲው ትግበራ ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው ሴክተሮችም ለትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ድጋፍ የሚያደርጉበትና ስራዎችን በየራሳቸው ዕቅዶች አካተው የሚተገበሩትን ሁኔታዎች ይመቻችላቸዋል።

ቀጣይነት ያለው የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ-ግብር ዘመናዊ ቴክኖሎጅን በመጠቀም የመረጃ ቅኝትና ዳሰሳ እንዲካሄድ እንዲሁም መረጃ ማጠናቀሪያ ሥርዓት እና አፈጻፀም መመሪያ እንዲዘረጋና እንዲጠናከር ይደረጋል።